**የፍትሐብሔር ጉዳዮች በተመለከተ ለጠቅላላ ትእዛዙ የተሰጠ ተጨማሪ መግለጫ (አደንደም)**
**በማርች 30፣ 2020 የተሰጠ**

የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ፍርድ ቤት ዋና (ቺፍ) ዳኛ፣ በአስቸኳይ ጊዜ ምክኒያት በተሰጠው ስልጣን መሰረት፣ በዚህ ወቅት ስላለው የማህበረሰብ ጤና አስቸኳይ ጊዜ በተመለከተ ማርች 18 ተሰጥቶ ማርች 19፣ 2020 የተሻሻለ ትእዛዝ ("የማርች 19 ትእዛዝ") አስተላልፎ ነበር። የጊዜ ገደቦች በተመለከተ የማርች 19 ትእዛዙ፣ በፍርድ ቤቱ ካልታዘዘ በስተቀር ከመይ 15፣ 2020 በፊት እንዲፈጸሙ በህጎች፣ በፍርድ ቤት ደንቦች፣ እና ፍርድ ቤት ባስተላለፋቸው እና በሌሎች ትእዛዞች የሰፈሩ የጊዜ ገደቦች የአስቸኳይ ጊዜ እስካለ ድረስ ይታገዳሉ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ይቆማሉ (ቶል ይደረጋሉ)፣ እንዲሁም ደግሞ ይራዘማሉ ይላል። የመይ 15 ቀን እንደሁኔታው ሊራዘም ይችላል።

በማርች 19 ትእዛዝ መሰረት የታገዱ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው የቆሙ (ቶል የተደረጉ)፣ እና የተራዘሙ የጊዜ ገደቦች የሚከተሉትና ሌሎችም ያካትታሉ፣ (1) ክስ ፋይል ለማድረግ የሚሰጠው ጊዜ (ስታቹ ኦፍ ሊሚቴሽንስ)፣ (2) ደንብ-ተኮር ቀነ-ገደቦች፣ ለምሳሌ የሰነዶች ማድረሻ ሂደት (ሰርቪስ ኦፍ ፕሮሰስ) የጊዜ ገደቦች፣ ለግኝት ጥያቄዎች ምላሽ መስጫ፣ እና ወደ ቅድመ-ክርክር (ፕሪትራያል) ኮንፈረንስ የሚመሩ ክስተቶች፣ እና (3) እንደነ የመርሐግብር ትእዛዞችና መከራከርያ ጽሁፍ ማቅረቢያ ትእዛዞች የመሳሰሉ ከማርች 18፣ 2020 በፊት የተሰጡ ጉዳይ-ተኮር ትእዛዞች።

አዲሱ የጊዜ ገደብ የሚወሰነው፣ ጊዝያዊው ከተፈጻሚነት ማቆሚያ (ቶሊንግ) ክፍለ ጊዜ በሚያበቃበት ቀን ነው፣ ይህ ቀን፣ በማርች 19 ትእዛዝ መሰረት፣ መይ 15 ነው። አዲሱ የጊዜ ገደብ በከፊል የሚወሰነው ቀነ ገደቡ እንዲኖር ያደረገው ክስተት የተፈጸመው ከማርች 18 በፊት ነው ወይስ በኋላ በሚል ይሆናል፣ እንደሚታወቀው ጊዝያዊ ከተፈጻሚነት ማቆምያ (ቶሊንግ) ክፍለ ጊዜ የተጀመረው ማርች 18 ነው። ጊዝያዊ ከተፈጻሚነት ማቆምያ (ቶሊንግ) ክፍለ ጊዜ ከመጀመሩ በፊት የተፈጸመ ክስተት የጊዜ ገደቡ በጊዝያዊ ከተፈጻሚነት ማቆምያ (ቶሊንግ) ክፍለ ጊዜ እንዲሆን ያደረገ ከሆነ፣ አዲሱ የጊዜ ገደብ እስከ ጊዝያዊ ከተፈጻሚነት ማቆምያ (ቶሊንግ) ክፍለ ጊዜ ድረስ ይራዘማል። ለምሳሌ፣ የሰነዶች ማድረሻ ሂደት (ሰርቪስ ኦፍ ፕሮሰስ)፣ ለግኝት ጥያቄዎች ምላሽ መስጫ፣ ወይም አቤቱታን ለመቃወም የተሰጠ የጊዜ ገደብ ጊዝያዊ ከተፈጻሚነት ማቆምያ (ቶሊንግ) ክፍለ ጊዜ ከተጀመረበት ማርች 18 አንድ ሳምንት ቀይቶ የነበረ ከሆነ፣ አዲሱ ቀነ ገደብ ጊዝያዊ ከተፈጻሚነት ማቆምያ (ቶሊንግ) ክፍለ ጊዜ ከተፈጸመ ከአንድ ሳምንት በኋላ ይሆናል። የጊዜ ገደቡን ያነሳሳው በጊዝያዊ ከተፈጻሚነት ማቆምያ (ቶሊንግ) ክፍለ ጊዜ ውስጥ የተፈጸመ ክስተት ከሆነ የሰአቱ ቆጠራ የሚጀምረው ጊዝያዊ ከተፈጻሚነት ማቆምያ (ቶሊንግ) ክፍለ ጊዜ በሚያበቃበት ቀን ይሆናል። ለምሳሌ፣ አንድ ከሳሽ ቅሬታው በማርች 18 እና መይ 15 መሀከል ፋይል ያደረገ ከሆነ፣ እና በRule 4(m)(1)(A) መሰረት መጥሪያውና ቅሬታውን ለተከሳሹ በ60 ቀናት ውስጥ ማድረስ የሚቻል ከሆነ፣ ከሳሹ ለተከሳሹ ከመይ 15 በኋላ ባሉ 60 ቀናት ውስጥ ማድረስ ይችላል ማለት ነው። አካሉ በRule 33(b)(2) መሰረት ለጥያቄዎች (ኢንተሮጋቶሪስ) በ30 ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠት ካለበት ወይም በRule 12-I(e) መሰረት ለአቤቱታ ምላሽ በ14 ቀናት ውስጥ መስጠት ካለበት ተመሳሳዩ መርህ ተግባራዊ ይሆናል።

በጊዝያዊ ከተፈጻሚነት ማቆምያ (ቶሊንግ) ክፍለ ጊዜ ምክኒያት፣ በማርች 19 ትእዛዝ መሰረት የሚተገበረው የተራዘመው የጊዜ ገደብ፣ የጉዳይዎ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ለጉዳይዎ ተገቢ ከሆነ፣ የጊዜ ገደቡ በተመለከተ አቤቱታ ፋይል ማድረግ አያስፈልግም። ነገር ግን፣ አንድ አካል የሚፈልገው የጊዜ ገደብ የማርች 19 ትእዛዝ ከሚሰጠው የጊዜ ገደብ የተለየ ከሆነ፣ የጊዜ ገደቡን ለማሳጠር ወይም ለማራዘም አቤቱታ ፋይል ማድረግ ያስፈልጋል።

ምንም እንኳን እርምጃው የሚወሰድበት የጊዜ ገደብ ባለው የአስቸኳይ ጊዜ ምክኒያት የታገደ፣ ጊዝያዊ ከተፈጻሚነት ማቆምያ (ቶሊንግ) የተደረገበት ወይም የተራዘመ ቢሆንም፣ የማርች 19 ትእዛዝ ማንኛውም አካል እርምጃ እንዳይወስድ አያግድም። በዚህ ክፍለ ጊዜ የፍትሐብሔር ክፍል ዳኞች በስምምነት በቀረቡ አቤቱታዎች ወይም በማርች 17፣ 2020 በስለው የነበሩ ተቃውሞ ያላቸው ወይም ከማርች 18፣ 2020 በኋላ ሙሉ በሙሉ የተብራሩ (ፉሊ ብሪፍድ) አቤቱታዎች ውሳኔ መስጠቱ ይቀጥላሉ።

ይህ ለጠቅላላ ትእዛዙ የተሰጠ ተጨማሪ መግለጫ (አደንደም) ሁኔታዎች በመቀየራቸው ምክኒያት እስኪሻሻል ወይም እስኪሰረዝ ድረስ በስራ ላይ ይቆያል።

የፍትሐብሔር ክፍል ዋና ዳኛ (ፕሪሳይዲንግ ጃጅ) በሰጡት ትእዛዝ በማርች 30፣ 2020 ተሰጠ።

[ተፈርሞበታል]

**ላውራ ኤ. ኮርዴሮ**
**ዋና ዳኛ (ፕሪሳይዲንግ ጃጅ)፣ የፍትሐብሔር ክፍል**